**ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ (አኢጋን)**

ሰኔ 12፣ 2004ዓም

# የኦሞ ሸለቆ ተወላጆች የመኖርና አለመኖር ጥያቄ!

## “ወደ ኦሞ መመለሳችን አይቀርም።...ከፈለጉም ባለንበት ሊገድሉን ይችላሉ።”

ከሰብዓዊ መብት ጥበቃ ዘገባ

ለታችኛው የኦሞ ሸለቆ ህዝብ የኦሞ ወንዝ የእትብታቸው መቀበሪያ፣ የመኖራቸው ምስጢር፣ የባህላቸው፣ የኑሮ መስተጋብራቸው፣ የማንነታቸው መሰረት የተተከለበት ነው። እነሱን ብቻ ሳይሆን የኦሞን ከንፈር ተከትለው ለሚኖሩ እስከ ኬኒያ በቱርካና ሃይቅ ዙሪያ ለሚገኙት በሙሉ ኦሞ የሰብዓዊ ዘር ብቻ ሳይሆን የብዝሃ ህይወት ዋስትናም ነው።

በያዝነው ዓመት ታህሳስ ወር እነዚህ ነዋሪዎች ለሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅት የደረሰባቸውን በደል ሲናገሩ በኩዌጉና በቦዲ ታርሶ ማሽላ የተዘራበትና ያሸተ ማሽላ ያለበት እርሻ በህወሃት/ኢህአዴግ ኃይሎች ተመንጥሮ በመጣሉ ህጻናትና አረጋውያን በአጠቃላይ ነዋሪ ምን ሊመገቡ እንደሚችሉ በመጠየቅ ገልጸው ነበር፡፡ ይህም የአቶ መለስ አገዛዝ እመራዋለሁ በሚለው ህዝብ ላይ እየለየ የሚፈጽመው ግፍ ከልክ አልፎ እየፈሰሰ ለመሆኑ ከማሳያዎቹ አንዱ ነው።

የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ ባለሥልጣናት ከብቶቻቸውን እንዲሸጡና ወደ ሰፈራ እንዲጠቃለሉ የሚነግሯቸው “ከእንግዲህ በኦሞ ወንዝ ላይ እጣ ፈንታ የላችሁም” በሚል ነው። አንድ የሙርሲ ተወላጅ በዚህ ዓመት የታህሳስ ወር **“አንድ ደጄ የማስረው ከብት አስቀርቼ የተቀሩትን እንድሸጥ ነገሩኝ”** ይላል አጥንት ዘልቆ የሚገባውን ግፍ ሲናገር፣ **“... በአንድ ከብት ምን አደርጋለሁ? እኔ ሙርሲ ነኝ። ረሃብ ሲመጣ የከብት አንገት በመብጣት ደም እጠጣለሁ፤ ሁሉንም ከብቶች ለገንዘብ ብለን ከሸጥን ምን እንመገባለን?”** ሲል በግራ መጋባት ይጠይቃል። ለዚህ የጨነቀው ወገን ጥያቄ መልሱ በኃይል አስገድዶ በጠመንጃ ማፈናቀል ሊሆን ይገባል?

**በትግራይ ተወላጆች ስም ወንጀል እፈጸመ ያለውን የህዝባዊ ወያኔ ሓርነት ትግራይን እንዲያወግዙና “በስሜ ወንጀል አትፈጽሙ” እንዲላቸው ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ሲወተውት የቆየው እንዲህ ያሉ ልብ የሚወጉ አሳዛኝ ድርጊቶች በየአቅጣጫው እንደሚፈፀሙ ማስረጃ ስለሚደርሰው ነው። “በደረቁ የበጋ ወቅት ችግር መምጣቱ አይቀሬ ነው። አሁን ውሃ አለ፤ ነገር ግን ውሃ በማይኖርበት ወቅት ወደ ኦሞ ወንዝ ተመልሰን የማንሄድ ከሆነ መንግስት ያለንበት ድረስ ውሃ እንዲያቀርብልን እንፈልጋለን። ይህንን ካላደረጉ እኛም ከብቶቻችንም እንሞታለን። ለማንኛውም ወደ ኦሞ መመለሳችን አይቀርም። ካልሆነም እንሞታለን!! ከፈለጉም ባለንበት ሊገሉን ይችላሉ።”** የሙርሲ ከብትአርቢ የተናገረውና ከሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅት ሪፖርት የተወሰደ ልብ የሚያስደቃ መልዕክት ነው።

**“መሬታችን ተወስዷል። መሬታችንን ተቀምተናል። መንግስት መሬታችንን በኃይል አስገድዶ ወሰደብን፣ ሁሉንም መሬታችንን ወስደውታል”** ሪፖርቱ በምስል ያስደገፈው የታችኛው ኦሞ ሸለቆ መንደረተኞች ዘር ማንዘራቸው ሲወርድ ሲዋረድ ከኖሩበት መሬታቸው ላይ ስለመፈናቀላቸው ካተተው ዘገባ ላይ የተወሰደው። ተገድደው እንዲኖሩ በሚወሰዱበት የሰፈራ መንደር ከብቶቻቸው እንዴት ሊኖሩ እንደሚችሉ የሚጠይቁም በርካታዎች ናቸው **“መንግሥት ውጡ፣ ሂዱ፣ ውጡ፣..... ይለናል። ነገር ግን እኛ የቡዲ ተወላጆች ቀዬአችንን ለቅቀን አንወጣም። ጉሮሯችንን እዚሁ ሊቆርጡት ይችላሉ። ከብቶቻችን እየተመገቡ ያሉት የአያቶቻችንን ከብቶች ሲመገቡ ነበሩትን ሳር**

**ነው። መንግስት ግንባር ለግንባር ሊያነጋግረን ይገባል”** ስትል የሚጠባ ልጅ ደረቷ ላይ ይዛ አስተያየት የሰጠች የኦሞ ሸለቆ ነዋሪ ተከትሎ **“... በሃይል ገብተው መሬታችንን መነጠሩት፣ ቀያችን ድረስ መጥተው ደኖችን መጨፍጨፍ ተያያዙ፣ ...”፡፡**

ቦታው የተመረጠው ከሰሜን እስከ ደቡብ በስኳር ንግድ ፍቅር በተጠናወተው የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ በአካባቢው የሚያከናውነው አዲስ የስኳር እርሻ ለአካባቢው ነዋሪዎችና ለአገሪቱ ህዝብ ይጠቅማል በሚል ቢሆንም ችግሩ ያለው ከተወለዱበትና ሲወርድ ሲዋረድ ከኖሩበት ምድራቸው ላይ እንዲፈናቀሉ የተፈረደባቸውን ወገኖቻችን ግን ማንም ሳያማክራቸው፣ ተመጣጣኝ ካሳ ሳይከፍላቸው መሆኑ አዲስ የወጣው የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ድርጅት (Human Rights Watch) ዘገባ ይናገራል። ሪፖርቱ ከተወለዱበት፣ ከኖሩበትና የማንነታቸው መሰረት ከተተከለበት ርስታቸው በአገዛዙ የጸጥታ ሃይሎች በሃይል አስገዳጅነት በማስፈራራት እንዲፈናቀሉ የተደረጉት የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ነዋሪዎች “ለምን” የሚል ጥያቄ ባቀረቡና ድርጊቱን በተቃወሙ ላይ ሰብዓዊ መብታቸውን በመጣስ ድብደባ፣ እስር፣ ማዋከብ ከመፈጸሙም በላይ በስፍራው የተሰማራው ቃኚ ሰራዊት ንብረታቸውን እንደሚዘርፍ ከብቶቻቸውን እንደሚገደሉና እንደሚሰረቁ ዋቢ በማጣቀስ ያትታል።

**“ረሃብ ከተከሰተ ምን ይውጠናል?”** በሚል ርዕስ ሰኞ ሰኔ 11፣2004ዓም ስጋቱን በማስቀደም የሰብዓዊ መብት ጥበቃ ያወጣውን ሪፖርት ተከትሎ የአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ ባሰራጨው መግለጫ **ለመላው የኢትዮጵያ ህዝብ፣ ወሳኝ ድጋፍ ለሚሰጡ ዓለም አቀፍ ለጋሽ አገራትና ተቋማት፣ ለተባበሩት መንግስታት፣ ለዓለም ባንክ፣ ለዓለም የገንዘብ ተቋም፣ ለዓለም አቀፍ ውሳኔ ሰጪ አካላት፣ ለውጪ አገር ባለሃብቶች፣ ለገንዘብ ተቋማት፣ ለንግድ ማህበረሰቦች፣ ለሲቪክ ማህበራት፣ ለማህበራዊ የፍትህ አካላት፣ ለሃይማኖት ተቋማትና ማህበረሰቦች፣.... አግባብነት ላላቸው አካላት በሙሉ በግፍ ከተፈጠሩበት ቀዬና የህልውናቸው መሰረት ከሆነው ምድራቸው ሰብዓዊ መብታቸው ተገፎ በግዳጅ እየተፈናቀሉ ላሉት ወገኖች ወትሮ ሲያደርገው እንደነበረው የድረሱላቸው ጥሪውን አሰምቷል። በተለየ መልኩ የጉዳዩን አሳሳቢነት ከኬንያ ጋር በማያያዝ ወደፊት በቀጠናው ሊፈጠር ስለሚችለው አደጋ ስጋቱን ይፋ አድርጓል።**

በተደጋጋሚ በተለያዩ አጋጣሚዎች የተማፅኖና የማስጠንቀቂያ መልእክታቸውን የሚያስተላልፉት የጋራ ንቅናቄያችን ዋና ዳይሬክተር አቶ ኦባንግ ሜቶ በሃይል እንዲፈናቀሉ የሚደረጉት የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ወገኖች የመጨረሻ እድል ፈንታ ምን ሊሆን ይችላል ሲሉ ስጋታቸውንና የስጋታቸውን መነሻ በማስረጃ ያቀርባሉ። **“ከ200 ሺህ በላይ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ነዋሪዎች፣ ከመኖሪያቸው፣ ከህይወታቸው ጋር ከተቆራኘው ውሃ፣ ከለመዱት የኑሮ ዘይቤያቸውና ከርስታቸው ላይ እንዲፈናቀሉ ሲደረግ ምን ሊከሰት ይችላል?”** ሲሉ ይህንን መግለጫ ለላኩላቸው አካላት በሙሉ ይጠይቃሉ።

“አገዛዙ አሁን እያደረገ ያለውን ተግባር ከልማት ጋር አያይዞታል ሆኖም በዓለም ዙሪያ እስከ 1.5 ሚሊዮን፤ በዋሽንግተን ዲሲ አካባቢ ደግሞ 300ሺህ ያህል ኢትዮጵያዊ ይገኛል በሚባልበት እስካሁን ከኦሞ ሸለቆ አካባቢ የማውቀው አንድ ሰው ብቻ ነው ያለው” በማለት ንጽጽራዊ አስተያየታቸውን የሰጡት አቶ ኦባንግ ሲቀጥሉም “200 ሺህ የኦሞ ሸለቆ ስደተኞች ወደየት ይሄዳሉ? ረሃብ ከሶማሊያ ለሃብ ያፈናቀሏቸው ስደተኞች ወዳጠለቀለቋት ኩኩማ የስደተኞች ካምፕ?” በማለት ይጠይቁና “የማይቻል፣ ተቀባይነት የሌለው” በማለት ይመልሳሉ። **አዲሲቷ የደቡብ ሱዳን ሪፖብሊክን ያነሳሉ። በደቡብ ሱዳን ውሉ ያለየለት የጎሳ ችግር እንዳለ ይጠቁሙና፣ እኒህ ከተፈጠሩበት ምድር እንዲባረሩ የተፈረደባቸው ወገኖች ወደ ደጋማው የኢትዮጵያ ክፍል ሊዛወሩ ይችሉ ይሆን? ይህም ጥያቄ ያስነሳል በማለት በበርካታ ምክንያቶች የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ተወላጆች ከተፈጠሩበት ምድር ውጪ ወደ የትም መሄድ እንደማይችሉ ያስረግጣሉ።**

**ካስቀመጡዋቸው ምክንያቶች በመነሳት አቶ ኦባንግ የኦሞ ሸለቆ ተወላጆች የመጨረሻ እጣ ፈንታ ለህልውና መፋለም ሊሆን እንደሚችል፣ ፍልሚያውም የመኖርና**

ያለመኖር የህልውና ሊሆን እንደሚሆን አበክረው ይናገራሉ። መራር የሆነው የጋራ ንቅናቄያችን ዋና ዳይሬክተር መልዕክት በቱርካና ሃይቅ ዙሪያ የሚኖሩትን 300ሺህ ከብት አርቢ አርሶ አደሮች ጨምሮ ከ200ሺህ በላይ የታችኛው ኦሞ ሸለቆ ነዋሪዎች የታጠቁ ናቸው። የህወሃት/ኢህአዴግ አገዛዝ እኒህን ወገኖች መግፋቱን ከቀጠለበትና በአግባቡ መያዝ ካልቻለ፣ ቀደም ሲል በኢትዮጵያና በኬኒያ ወሰን የነበረው በቋፍ ላይ ያለ አለመግባባት የታከለበት ግጭት ሊነሳ እንደሚችል በጥብቅ አሳስበዋል። ለረዥም ዓመታት መልስ ያላገኘው የሱዳንና ኬንያ ድንበር ውዝግብና በኬንያና በኢትዮጵያ ድንበር እየተካሄደ ያለው የነዳጅ ፍለጋ ስጋት ላይ የጣላቸው የታጠቁ ከ500ሺህ በላይ ነዋሪዎች ጉዳይ ተዳምሮ የቀጣናውን ጂኦፖሊቲካና ጸጥታ የሚፈታተን አደጋ እንዳይከሰት ጥሪ አሰተላልፈዋል።

በበርካታዎቻችን ዘንድ ከኢትዮጵያዊነታቸው ይልቅ የቱሪዝም መስህብነታቸው ጎልቶ የሚታየው የታችኛው ኦሞ ነዋሪዎች ህይወት አፋፍ ላይ ደርሷል፡፡ ከአኗኗራቸው ልዩ መሆን በመነሳት በሰብዓዊ ፍጡርነታቸው የመከበራቸው ሁኔታ የአብዛኛው ኢትዮጵያዊ ቀልብ የማይስበውን የእነዚህ ወገኖቻችን መጻዒ ዕድልና እንደ ሰው እንዲሁም እንደ አንድ ማኅበረሰብ የመኖራቸው ህልውና ጫፍ ላይ ነው፡፡ ለዘመናት ቅጠል በሌለበት በረሃ በመቆየቱና ትግል የጀመረበት ክልል አረንጓዴ አለመሆን እልህ ውስጥ ያስገባው የሚመስለው ህወሃት የትግራይን ተራሮችና ኮረብታዎች በደን ለማልበስ ቀን ተሌት ሲተጋ በተፈጥሮ ደን የተሸፈኑትንና በተባበሩት መንግሥታት በዓለም ቅርስነት የሚታወቁ፤ ዘመናቸው ተቆጥሮ የማያበቃ የኢትዮጵያ ደኖችን ለማውደምና አረንጓዴ የለበሰውን የኢትዮጵያ ክልል ወደ በረሃነት ለመለወጥ የሚያደርገው ጥድፊያ በቅድሚያ በትግራይ ተወላጆች ሊገታ ይገባዋል እንላለን፡፡ ትግራይን ከበረሃነት ወደ አረንጓዴነት ለማሸጋገር የጋምቤላ ደን መጨፍጨፍ የለበትም፤ የኦሞ ሸለቆ የተፈጥሮ ኃብት መሟጠጥም የለበትም፡፡ ሁሉም የኢትዮጵያ ክልል መሆኑን ለሚያምን ልማቱን ደን ሳይጨፈጭፍ ማከናወን ይችላል፡፡ አንዱን ክልል በደን ለመሸፍ ሌላውን ክልል በረሃማ ማድረግ ምንም ዓይነት አስፈላጊነትም ሆነ ጠቀሜታ የለውም - ጥላቻንና ቂምን ከመፍጠር በቀር፡፡ አንዱን ክልል ለማልማት ሌላውን ማራቆት ሌላ ድብቅ አጀንዳ ከሌለው በስተቀር በምንም ዓይነት ስሌት ጥቅሙን ማስረዳት አይቻልም፡፡ የጋራ ንቅናቄያችን መሪ መመሪያ ሰብዓዊነት እንደመሆኑ ለኦሞ ሸለቆ ነዋሪዎች መብት መከበር ስንሟገት አሁን በልማት ስም እየተደረገ ያለው ድርጊት ጊዜውን ጠብቆ የትግራይ ተወላጆችን አስከፊ ችግር ላይ እንደሚጥላቸው ሳናስጠነቅቅ ማለፍ ስለማንችል ነው - አንዱ ሲነካ ሁሉም ይነካል!!

## ለአዲሲቷ ኢትዮጵያ የጋራ ንቅናቄ

*****************************************************************************************************

*ለዚህ ደብዳቤ ምላሽም ሆነ ለተጨማሪ መረጃ ለአኢጋን ሚዲያና ሕዝብግንኙነትን ግብረኃይል (media@solidaritymovement.org) በመጻፍ ወይም ድረገጻችንን (www.solidaritymovement.org) በመጎብኘት ለመረዳት ይችላሉ፡፡*

